ለአንዳንድ አዋቂዎች ከጃንዋሪ 1/2026 ጀምሮ በ ዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ፕሮግራም ላይ ለውጥ የሚደረግ ይሆናል! እነዚህ ለውጦች የዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ተጠቃሚ በሆኑ ሕፃናት ወይም ነፍሰጡሮች ላይ ተፅዕኖ አያሳድሩም። የበለጠ መረጃ ለማግኘት ሜዲኬድ (Medicaid) የጤና እንክብካቤ ሽፋን ለውጥ (2025)ይጎብኙ። በርካታ አዋቂዎች በአዲሱ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ሽፋን የሚደረግላቸው ሲሆን አብዛኞቹን ተመሳሳይ ጥቅማጥቅሞችን መልሰው የሚያገኙ ይሆናል። ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም እርዳታ ከፈለጉ፣ በስልክ ቁጥር (202) 724-7491 / TTY 711 ወይም በ (877) 685-6391 ላይ ለጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ተቋም (Health Care Ombudsman) ይደውሉ ወይም በኢሜል አድራሻ:-healthcareombudsman@dc.gov ላይ መልዕክት ይላኩ።

አሁን ምን ማድረግ ይችላሉ:-

- የመልዕክት ሳጥንዎን እና በ districtdirect.dc.gov ላይ ያለውን የዲስትሪክት ዳይሬክት መለያዎን (District Direct account) ያረጋግጡ። DHCF በሴፕቴምበር አጋማሽ ላይ በዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ፕሮግራም ላይ ስለተደረጉ ለውጦች የሚመለከት የማሳወቂያ መልዕክት ልኳል። የዲስትሪክት ዳይሬክት (District Direct) ድር ጣቢያዎን ወይም መተግበሪያዎን በመጠቀም የእርስዎን ሁኔታ ማረጋገጥ ይችላሉ።
- የእውቂያ መረጃዎን (contact information) ያዘምኑ። የእውቂያ መረጃዎን (contact information) ለማዘመን ወደ ዲስትሪክት ዳይሬክት (District Direct) ይግቡ። ሁሉም የማሳወቂያ መልእክቶች በፖስታ ይላካሉ። DHCF ትክክለኛ የእውቂያ መረጃ (contact information) ከሌለው፣ ስለ ሽፋንዎ የሚመለከቱ ጠቃሚ የማሳወቂያ መልዕክቶች አይደርሱዎትም።
- ሜዲኬድዎን (Medicaid) በሰዓቱ ያድሱ። አሁንም የዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ሽፋን ተጠቃሚ ከሆኑ፣ የእድሳት ቀንዎን ይወቁ እንዲሁም በሰዓቱ ያድሱ። የማደሻ ጊዜው ሲደርስ ከ DHCF የማሳወቂያ መልዕክት ይደርስዎታል። በዲስትሪክት ዳይሬክት (District Direct) በኩል በመስመር ላይ (online) ማደስ ይችላሉ - የዲሲ ሜዲኬድዎን (DC Medicaid) ለማደስ በአካል መሄድ አይጠበቅብዎትም።
- ስለ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan)ይወቁ። በሜዲኬድ (Medicaid) ተጠቃሚ ለመሆን ገቢዎ በጣም ከፍተኛ ከሆነ ለአዲሱ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) መጠነኛ ገቢ ላላቸው የ DC ነዋሪዎች ጥራት ያለው የጤና ሽፋን የሚያቀርብ ነው። ሽፋን ላገኘ እንክብካቤ ምንም ዓይነት ወርሃዊ አረቦን እና ከኪስ የሚከፈል የገንዘብ ወጪ አይኖርም። ሁሉም ፕላኖች የዶክተር ጉብኝቶችን፣ አስቸኳይ የእንክብካቤ ጉብኝቶችን፣ የሆስፒታል ቆይታዎችን፣ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችን፣ የአእምሮ ጤና እንክብካቤን እና ሌሎችንም አገልግሎቶች ይሸፍናሉ።

በተደጋገሞ የሚነሱ ጥያቄዎች

ከጃንዋሪ 1/2026 ጀምሮ፣ በዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ፕሮግራም ላይ ለውጦች ይደረጋሉ።

- ጃንዋሪ 1/2026 ላይ ምን ይለወጣል?
  - በወላጅ/በተንከባካቢ ዘመድ የሜዲኬድ (Medicaid) ምድብ ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች የገቢ ጣሪያ በፌደራሉ የድህነት እርከን (FPL) ከ 221% ወደ 138% ዝቅ እንዲል ይደረጋል።
  - ልጅ በሌላቸው አዋቂዎች ሜዲኬድ (Medicaid) ምድብ ውስጥ ለሚገኙ ግለሰቦች የገቢ ጣሪያ በፌዴራሉ የድህነት እርከን (FPL) ከ 215% ወደ 138% ዝቅ እንዲል ይደረጋል።
  - በ FPL ከ 138% በላይ ሆነው የሜዲኬር (Medicare) ተጠቃሚ የሆኑ ወላጆች/ተንከባካቢ ዘመዶች ወይም ልጅ የሌላቸው አዋቂዎች ወደ ብቁ የሜዲኬር ተጠቃሚ (Qualified Medicare Beneficiary (QMB)) ፕሮግራም ብቻ የሚሸጋገሩ ይሆናል።

    - ከሜዲኬድ (Medicaid) ወደ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ወይም ዲሲ ሄልዝ ሊንክ (DC Health Link) የሚደረግ ሽግግር።

- ስለእነዚህ ለውጦች በተመለከተ የማሳወቂያ መልእክት ወይም ደብዳቤ ይደርሰኛል?
    - አዎ፣ መረጃ የያዘ ማሳወቂያ/ደብዳቤ በሴፕቴምበር አጋማሽ ላይ ተልኳል። ስለ ሜዲኬድዎ (Medicaid) ማብቂያ በተመለከተ ሌላ የማሳወቂያ መልዕክት በዲሴምበር ወር መጀመሪያ ላይ በፖስታ ይላካል። እንዲሁም የማሳወቂያው መልእክቱን በዲስትሪክት ዳይሬክት መለያ (District Direct account) ላይ ማየት ይችላሉ። ይህ የ FAQ ሰነድ በቀጣይ የሚደረጉ ለውጦችንም ይዳስሳል።

- በሜዲኬድ (Medicaid) ፕሮግራም ውስጥ ለሚገኙ ወላጅ/ተንከባካቢ ዘመድ እና ልጅ የሌላቸው አዋቂዎች የአሁኑ እና አዲሱ የገቢ ጣሪያ ምን ያህል ነው?
    - ከጃንዋሪ 1/2026 ጀምሮ፣ የወላጅ/ተንከባካቢ እና ልጅ የሌላቸው አዋቂዎች ፕሮግራም የገቢ ጣሪያ ከፌዴራሉ የድህነት እርከን ወደ 138% (5% ገቢን ሳያካትት) ዝቅ ይደረጋል። እባክዎን ወቅታዊ እና የቀጣይ የገቢ ጣሪዎችን ከዚህ በታች ይመልከቱ።
    - በቤተሰብ መጠን ላይ የተመሰረቱ ተጨማሪ ጣሪያዎችን ለማግኘት እባክዎን የ DHCF ድር ጣቢያን በሜዲኬድ (Medicaid) የጤና እንክብካቤ ሽፋን ለውጦች (2025)ላይ ይጎብኙ።

- ገቢዬ ከአዲሱ የገቢ ጣሪያዎች መጠን (ከፌዴራል የድህነት እርከን 138%) በላይ ከሆነ ከ 01/01/2026 ጀምሮ ምን ይከሰታል?
    - የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎ በ 12/31/2025 ላይ የሚቋረጥ ይሆናል። በዲሴምበር ወር መጀመሪያ ላይ መቋረጡን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርስዎታል።
    - ገቢዎ በ FPL ከ 138% በላይ ከሆነ እና ከ 1/1/2026 በኋላ የሚያመለክቱ ወላጅ/ተንከባካቢ ወይም ልጅ የሌልዎት አዋቂ ከሆኑ፣ ለሌሎች የጤና እንክብካቤ ሽፋን አማራጮች ብቁ ስለመሆንዎ ለማወቅ ይገመገማሉ።

- ከሜዲኬድ (Medicaid) በተጨማሪ ሌላ ምን ዓይነት የጤና እንክብካቤ አማራጮች አሉ?
    - የሚከተሉት በዲስትሪክቱ ውስጥ በነፃ ከሚገኙ እስከ በዝቅተኛ ወጪ ማግኘት የሚችሏቸው የጤና ሽፋን አማራጮች ናቸው። እባክዎን እያንዳንዱ ፕሮግራም የገቢ ጣሪያ እና ሌሎች የብቃት መገምገሚያ መስፈርቶች እንዳሉት ልብ ይበሉ።
        - Medicare ላላቸው እና ብቁ ለሆኑ ሰዎች ዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ኳሊፋይድ ሜዲኬር ቤነፊሽሪስን (Qualified Medicare Beneficiaries (QMB)) ያቀርባል
        - ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan)፣ ከጃንዋሪ 1/2026 ጀምሮ የሚጀመር አዲስ ሽፋን ነው። ይህ ፕላን ዕድሜያቸው ከ 21-64 ዓመት ለሆኑ እና በፌዴራል የድህነት እርከን ከ 138% እስከ 200% ዓመታዊ የገቢ መጠን ላላቸው ግለሰቦች የቀረበ ነው። ለበለጠ መረጃ፣ ለሄልዚ ዲሲሰ ፕላን (Healthy DC Plan) ብቁ የሚያደርጉ የገቢ መጠኖችንይመልከቱ።
- ሄልዚ ዲሲሰ ፕላን (Healthy DC Plan) ለማግኘት የሚከፈሉ ክፍያዎች አሉ?
    - የሉም። ሄልዚ ዲሲሰ ፕላን (Healthy DC Plan) ወርሃዊ ክፍያዎች (አረቦን ተብሎም ይጠራል) ወይም ሽፋኑ ላገኙ አገልግሎቶች ከኪስ የሚከፈሉ ክፍያዎች የሉትም። በፕሮግራሙ ከሚሳተፉ ሐኪሞች እና

ሆስፒታሎች፣ እንዲሁም የማህበረሰብ ጤና ማእከሎች እንክብካቤ ሲያገኙ ከኪስ የሚከፈሉት ሌላ ክፍያ አይኖርም።

- ዲሲ ሄልዚ ሊንክ (DC Health Link) ያስከፍላል?
    - አዎ። የዲሲ ሄልዚ ሊንክ ፕላን (DC Health Link's Plan) ማዛመጃ መሳሪያን በመጠቀም:-
        - ለዝቅተኛ ወርሃዊ አረቦን እና ዝቅተኛ ከኪስ ለሚከፈል ወጪ ብቁ መሆን አለመሆንዎን ይወቁ
        - የፕላኑን ባህሪያት፣ ጥቅማጥቅሞችን እና ወጪዎችን ጎን ለጎን በማድረግ ያወዳድሩ o ሐኪምዎ በፕላኑ አውታረ መረብ ውስጥ የታቀፉ መሆን አለመሆናቸውን ያረጋግጡ
        - በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶችዎ በፕላኑ የተሸፈኑ መሆን አለመሆናቸውን ይመልከቱ

- የሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ሽፋን መቼ ይጀምራል?
    - የሄልዚ ዲሲ ፕላን ሽፋን (Healthy DC Plan coverage) ከ 01/01/2026 ጀምሮ በስራ ላይ ይውላል

- የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋኔን ካጣሁ እና ለሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ብቁ ከሆንኩ፣ በዚህ የሽግግር ወቅት ምን እርምጃዎችን መውሰድ አለብኝ?
    - የሜዲኬድ (Medicaid) ብቁነት መስፈርት በመቀየሩ ምክንያት የ ሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎን ካጡ፣ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ወዲያውኑ በሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ስር ይመዘግብዎታል። የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎ በዲሴምበር 31/2025 ያበቃል። የሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ሽፋንዎ በጃንዋሪ 1/2026 ይጀምራል። በሽፋንዎ ላይ ክፍተት አይፈጠርም።
    - የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎ በ AmeriHealth Caritas DC ወይም በ MedStar Family Choice ስር ከሆነ፣ አሁን ያልዎት የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎ በሚገኝበት ኩባንያ ስር ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ወዲያውኑ ለሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ይመዘግብዎታል። ምንም እንኳን የሚያገኙት ጥቅማጥቅሞች እና አንዳንድ የአገልግሎቱ አቅራቢዎች የተለያዩ ቢሆኑም፣ አዲሱን ሽፋንዎን የሚያቀርበው ኩባንያ ግን እራሱ የበፊቱ ኩባንያ ይሆናል።
    - የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋንዎ የሚገኘው Wellpoint DC ጋር ከሆነም፣ ሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ወዲያውኑ ለሄልዚ ዲሲ ፕላን (Healthy DC Plan) ይመዘግብዎታል።

| አሁን ላይ ያልዎት የጤና ፕላን... | ወዲያውኑ በ... |
|---|---|
| AmeriHealth Caritas Medicaid MCO ከሆነ | በ AmeriHealth Caritas Healthy DC Plan ስር ይመዘገባሉ |
| Medstar Family Choice Medicaid MCO ከሆነ | በ Medstar Family Choice Healthy DC Plan ስር ይመዘገባሉ |
| Wellpoint Medicaid MCO ከሆነ | በ CareFirst BlueCross BlueShield Healthy DC Plan ስር ይመዘገባሉ |

- ሜዲኬር (Medicare) ካለኝ፣ በዚህ የሽግግር ወቅት ምን እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርብኛል?
    - ሜዲኬር (Medicare) ካልዎት እና ገቢዎ በ FPL ከ 138% በላይ ከሆነ፣ ዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) ወደ ኳሊፋይድ ሜዲኬር ቤነፊሸሪ (Qualified Medicare Beneficiary (QMB)) ፕሮግራም ያስተላልፍዎታል። QMB-ብቻ ሙሉ የሜዲኬድ (Medicaid) ሽፋን አይደለም ነገር ግን የክፍል A እና ክፍል B አረቦን እና የሜዲኬር (Medicare) የወጪ መጋራት የጋራ ክፍያዎችን፣ የጋራ ኢንሹራንስን እና ተቀናሾችን ለመክፈል እርዳታ ያቀርባል።

- እነዚህ ለውጦች የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ እንክብካቤን በተመለከተ በወላጅ/ተንከባካቢ ዘመድ ወይም ልጅ በሌላቸው አዲስ ነፍሰጡር አዋቂዎች ላይ ምን ተፅዕኖ ያሳድራሉ?
    - ሜዲኬድ (Medicaid) የ 12 ወራት የድህረ ወሊድ እንክብካቤን ጨምሮ በወሊድ ጊዜ የሚኖር ወጪን ይሸፍናል።

ወደ ዲስትሪክት ዳይሬክት መለያዎ (DISTRICT DIRECT ACCOUNT) እንዴት መግባት ይችላሉ

በዲሲ ሜዲኬድ (DC Medicaid) በኩል የጤና እንክብካቤ ሽፋን ካልዎት፣ ጠቃሚ መረጃ እንዳያመልጥዎት። እስካሁን ካላደረጉት፣ ጊዜ ወስደው አድራሻዎን፣ ስልክ ቁጥርዎን እና/ወይም የኢሜል አድራሻዎን በ districtdirect.dc.gov ላይ ዛሬውኑ ያዘምኑ።

መረጃዎን ለማዘመን፣ በመጀመሪያ በ districtdirect.dc.gov ላይ መለያ ይፍጠሩ ወይም Google Play አሊያም Apple App Store ውስጥ የሚገኘውን የ District Direct የሞባይል መተግበሪያን ማውረድ አለብዎት።

የ District Direct መለያን እንዴት መፍጠር ይቻላል

1. በዋናው ገጽ ላይ "Login" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ እና ከዚያም "Create Account" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።
2. በሚቀጥለው ገጽ ላይ፣ እንደ የተጠቃሚ ስም (username) እና የይለፍ ቃል (password) ያሉ መለያዎን ለመፍጠር የሚያስፈልጉ መረጃዎች ያስገቡ።
3. አንዴ ይህን አድርገው ካጠናቀቁ በኃላ "Create Account." የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። ከዚያም በመነሻ ገፁ (homepage) ላይ አስፈላጊውን መረጃ በመሙላት "Connect
4. Your Account" የሚለውን ጠቅ በማድረግ መለያዎን ያገናኙ።
5. መለያዎ አንዴ ገባሪ (active) ሲሆን፣ መረጃዎን ወደሚያሳየው፣ የመነሻ ገፅ (homepage) ይመለሱ።

ወደ ዲስትሪክት ዳይሬክት መለያዎ (District Direct Account) እንዴት መግባት ይችላሉ

1. መለያ ካልዎት፣ በ districtdirect.dc.gov ላይ ወይም የ District Direct ሞባይል መተግበሪያ (ከ Google Play እና Apple App Stores በማውረድ) መለያዎ ላይ መድረስ ይችላሉ።
2. በመቀጠል፣ የተጠቃሚ ስምዎን (username) እና የይለፍ ቃልዎን (password) ማስገባት አለብዎት። ከዚህ ቀደም ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት በመስመር ላይ (online) ካመለከቱ፣ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ባመለከቱበት ወቅት የተጠቃሚ ስምዎን (username) እና የይለፍ ቃልዎን (password) ፈጥረዋል።
3. የተጠቃሚ ስምዎን (username) እና የይለፍ ቃልዎን (password) ካላስታወሱ "የይለፍ ቃል ረሳሁ" (“Forgot Password”) ወይም "የተጠቃሚ ስም ረሳሁ" (“Forgot Username” ) የሚለውን አገናኝ ጠቅ በማድረግ ወይም ለ District Direct የደንበኞች አገልግሎት በስልክ ቁጥር (202) 727-5355 ወይም TTY 711 በመደወል ዳግም ማስጀመር ይችላሉ።